በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ  አሀዱ አምላክ አሜን

ከጥንቱ፡ አንዲት ሃይማኖት ነበረች ኤፌ 4:5 እሷም  በክርስቶስ ደም የተመሰረተችው አንዲት ኦርቶዶክስ ተዋህዶ መሆኗ ለኢትዮጵያ ሰዎችና ኢትዮጵያን የሚያውቋትም የእውቀታቸውን መንገድ የሚጀምሩት በቤተ ክርስቲያኖች ቅርስ ነው ምሳሌ ላሊበላ ቤተክርስቲያን በ 13ኛ ክ/ዘመን በቅዱስ ላሊበላ ከአንድ ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሰራው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያንና ሌሎችም ቋሚ ምስክሮች ናቸው ለሁሉም አይንን ከፍቶ ካዩት ልብን ከፍተው ካስተዋሉበት ያሉት ሁሉ ጥሩ አስተማሪዎች መስካሪዎች ናቸው።

እንዲሁም በሌላው ሰው መሠረት ላይ እንዳልሰራ የክርስቶስ ስም በተጠራበት ስፍራ ሳይሆን ወንጌልን ለመስበክ ተጣጣርሁ ሮሜ15:20 ታዲያ ከዚህ ቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ምን እንማር ይሆን? ንጉሥ ሱሶንዮስ ነበሩ ፖርቱጋሎች የኢትዮጵያ ሃይማኖቷ ካቶሊክ እንዲሆን ባሏቸው ጊዜ ለኢትዮጵያ ስለክርስትና ማስተማር ሳይሆን ስለክርስትና ከኢትዮጵያ መማር ትችላላችሁ እውነት ስለክርስትና ከሆነ ዓላማችሁ ኢትዮጵያውያን ሳይሆኑ ስለ ክርስቶስ የማያውቁ ያልሰሙ በጣኦት ወደሚያመልኩ ወደቻይናና ወደ ጃፓን ሂዱ ያሏቸው ከላይ የተጠቀሰውን ጥቅስ ነበር በግልጽ የተናገሩት ሀሰተኛ ነቢያት ሀሰተኛ ክርስቶሶች ይመጣሉና ተጠንቀቁ ሆኖም የፀና ይድናል ብሎ ጌታችን አምላካችንና መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ተናግሯል እኛም በዚሁ አምላካዊ ቃል መሰረት ነቅተን ዲያብሎስንና የሱን ስራ አስፈፃሚዎችን ልንቃወም መልስ ልንሰጣቸውና ብዙዎቻችን በስሜታዊነትና ጠልቆ ባለማወቅ ወደስህተት እንዳንሄድ "ነገር ግን ወንድሞች ሆይ እናንተ የተማራችሁትን ትምህርት የሚቃወሙትን መለያየትንና መሰናከያ የሚያደርጉትን ሰዎች እንድትመለከቱ እለምናችኋለሁ ከእነርሱ ዘንድ ፈቀቅ በሉ እንዲህ ያሉት ለገዛ ሆዳቸው እንጂ ለጌታችን ለኢየሱስ አይገዙምና በመልካምና በሚያቆላምጥ ንግግርም ተንኮል የሌለባቸውን ሰዎች ልብ ያታልላሉ" ሮሜ16:17 ከአታላዮች ለመዳን፣ለመጠበቅ እንችል ዘንድ ሰይጣን ሰራዊቱን በቤተክርስቲያን ውስጥና በውጭ አሰማርቶ ስለሚገኝ መልስ እንሰጥ እንችል ዘንድና ወደስህተት ከመግባት እንጠበቅ ዘንድ ይህች ጽሁፍ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ባፈራቻቸው ልጆቿ በሆኑት በማህበረ ማርቆስ ወጥቷል። ወደፊትም እውነተኛ የተዋህዶ ልጆች ከሆኑት ጋር በመተባበር እንደ እግዚአብሄር ፈቃድ ብዙ እቅዶች ስለአሉ ከእቅዶቹም አንዱ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነቷን ክርስትናዊ ባህሏንና ሥርዓቷን ተጠብቆ እንዲኖር ለማድረግ ቋንቋችን የሆነውን ግዕዝን ተምሮ ለማስተማርና ለማቆየት በአሁኑም ሰዓት ማህበሩ የዉጭ ዜጎችን ያቀፈ ሲሆን አሜሪካኖችን የካሪቢያን ደሴት ሀገሮችን በተቻለ ሁሉ በእንግሊዘኛም ስለ እምነታችን በመጻፍና በማስተማር መቀጠል የሚሉት ናቸው።

ማሳሰቢያ ይህ ጽሁፍ ከተለያዩ በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እምነት ደንብና ሥርዓት መሰረት ከተጻፉ መጽሀፍት የተውጣጣ ሲሆን ቀዳሚ የሆነውም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ለማፍረስ በውስጥና በውጭ በፈረንጅ ዱቄትና ገንዘብ ተታለው በተንቅሳቀሱት ላይ አስፈላጊውን በማድረግ ሰይጣናዊ ሥራቸውን ካጋለጠው ውድ የተዋህዶ አርበኛው ከሆነው ከወጣት ብርሀኑ ጎበና ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የጀርባ አጥንት ከነበሩት ከውድ የተዋህዶ አባት ከብፁዕ አባታችን ከአቡነ ጎርጎርዮስ የሸዋ ሊቀ ጳጳስ ከአስራት ገ ማርያም ከሰማንያ አሀዱ መጽሀፍ ቅዱስ የተወሰደ መሆኑን በትህትና እገልጻለሁ ለማባዛትና ለመጠረዝም የረዱኝ በዲሲና አካባቢው የሚኖሩ የኪዳነ ምህረት የጽዋ ማህበር አባላት ሲሆኑ በጽሁፍ በኩል የረዳኝን ዲያቆን ዮናታን አመዘነን እግዚአብሄር ሀይሉን ብርታቱ ይስጣቸው ማህበራቸውንም ያሰፋ ዘንድ የዘወትር ጸሎቴ ነው።

እግዚአብሄር ሀገራችንን ኢትዮጵያንና ውድ ቤተ ክርስቲያናችንን ይጠብቅልን የእመቤታችን የቅድስተ ቅዱሳን የድንግል ማርያም የቅዱሳን መላእክት የቅዱሳን አባቶቻችን ጸሎት ምልጃና በረከት አይለይን አሜን

ጥያቄ ካለዎት ዲያቆን ካሳሁን ገ/ሥላሴ

ስልክ (301)585-6119

E-mail: kassahun@erols.com

"ወስብሀት ለእግዚአብሄር"

4ኛ. የቅዱሳን አማላጅነት በመስቀሉ ተ በምሰኝ ንጉሥታችን ይትር ሊሆሰሰን ይችላል

1. ከመሞታቸው በፊት

ዘፍ 18፡ 22-23
ዘፍ 20፡ 7, 17
ዘፀ 32፡ 10, 14
ዘኁ 14፡ 19-14
1ኛ ነገሥ 13፡ 4-6
ሮሜ 5፡ 19
1ኛ ቆሮ 4፡13
2ኛ ቆሮ 5፡ 20
2ኛ ቆሮ 9፡ 14
ኤፌ 1፡ 15-17
2ኛ ነገሥ 19፡34, 20፡6
ኢዮብ 42፡ 7-10
መዝ 105፡ 21-22
መሣ 65፡ 8
ኤር 42፡ 1-12
2ኛ ተሰ 1፡ 11-12
ያዕ 5፡ 14-18

2. ከሞቱ በኋላ በዐፀደ ነፍስ ያሉ ሰዎች እንደመላእክት ስለሆኑ ያማልዳሉ::

ሀ/ - ሄኖክ 9፡ 21-23 × 1ኛ ሳሙ 28፡3-20.
- ሄኖክ 12፡ 33-39
- ሉቃ 1፡ 48-50
- ራእይ 6-9-11

ለ/ መላእክት እንደሚያማልዱ

- ዘካ 1፡ 12፡ 17
- ዳን 12፡ 1
- መዝ 33፡ 6

3. ለቅዱሳን ቃል ኪዳን ከሰተሰጠ መታሰቢያቸው ለዘለዓለም ይኖራል:: በስማቸውም መታሰቢያ ለሚያደርግ ምሕረት ያደርግለታል:: ዋጋውም አይጠፋ፣ ትም ይሁን ለመረዳት የሚከተለውን ያንብቡ::

ሀ/ በለቃል ኪዳን

- መዝ 88፡ 1-3
- መዝ 110፡ 4-5
- መዝ 111፡ 6
- ሉቃ 1፡ 50
- ሉቃ 1፡ 54-55
- ሉቃ 1፡ 72-73
- 2ኛ ቆሮ 5፡ 19-20
- ዕብ 6፡ 9-10

ለ/ ጌታ በአዲስ ኪዳን ከገባላቸው ቃል ኪዳን በጥቂቱ እንጠቅሳለን::

- ማቴ 10፡ 40-42
- ማቴ 19፡ 28
- ዮሐ 20፡ 23
- ራዕይ 3፡ 21

ቅድስት ቤተክርስቲያን /ሰማያዊቷ ቤተመቅደስ/

የቅድስት ቤተክርስቲያን አመሠራረቷ ታሪካዊ አመጣጡ

በብሉይ ኪዳን — በአዲስ ኪዳንም በሆነ ጌታችን ለሰውም

ዘጸ 25፡8 — 5፡ 17 — የሐዋ 3፡ 1

3. እግዚአብሔር ፍርዱን ለእያንዳንዱ የሚሰጠው እንደሥራው ነው

– ሮሜ 2፣ 6 – ማቴ 7፣ 21
– 2ኛ ቆሮ 5፣ 10 – ራእይ 22፣ 12

እምነት በገለ ክንፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማና
የውንም ነገር የሚያስረዳ ነው፡፡ /ዕብ 11፣1.

× ይህ እምነት ሃይማኖት ይባላል ሃይማኖትም አንዲት ናት
/ኤፌ 4፣5/
በዚህ እምነታችንም መለካም /በግ/ ከሠራንባት ማለት ከከጎ
ሥራ ካዋሐድናት፣ በሥራ ካገለጥናት እንድናለን፡፡
– ሃይማኖት ብለን የምንለው የክርስትና እምነትና የቤተክ
ርስቲያን ትምህርት ከዚህ እንደሚከተለው በየርዕሱ ተዘ
ርዝሯል፡፡

## ስግደት

1. ስግደት የሚፈፀምበት ቦታ ቤተመቅደስ ባለበት ሁሉ ነው፡፡
በአገር አይወሰንም

| | | |
|---|---|---|
| ዘፀ 33፣ 11 | መዝ 28፣ 2 | ዮሐ4፣19–24 |
| 2ኛሳሙ 12፣ 20 | 3ዝ95፣ 9 | ዮሐ12፣20 |
| 1ኛ ዜና መዋ 16፣ 29 | መዝ 137፣ 1–2 | የሐ ዋ8፣ 27 |
| መዝ 5፣ 7 | ሐዝ 46፣ 1–4 | ራእይ 11፣1–3 |

2. ስግደት የሚሰገደው በእግዚአብሔር ነው ለጌታ አምላካችን ነው፡፡

| | |
|---|---|
| ኢሳ 45፣ 2 | ዘዳግም |
| ማቴ 4፣ 10 | ዕብ 1፣6 |
| ፊሊጵ 2፣ 10 | ራእይ 7፣ 11 |

3. የእግዚአብሔር ቃል የመጣላቸው ቅዱሳን /የፀጋአማለከት/ና ቸው፡፡

| | |
|---|---|
| ዘጸ 4፣16–17 | ዮሐ 10፣31–36 |
| ዘጸ 7፣ 1 | 1ኛ ቆሮ 6፣1–2 |
| መዝ 81፣ 6 | ራእይ 3፣21 |
| ማቴ19፣ 26–29 | |

4. ይህን ያህል ሳለበረከት አምላክነትን ለማጣ ጥ/ጹሉ ለመፀለ ምኅ/የፀጋ ሰገደት ይገባል::

ሀ. ለእመቤታችን
መዝ 44፡12-13
ኢሳ 49፡23
ኢሳ 60፡14
ሉቃ 1፡41

ለ. ለቅዱሳን መላእክትና ለሰዎች 1ኛ ዜና መ 21፡ 21
ዘፍ 27፡29
ዘፍ 33፡6
ዘፍ 42፡6
1ኛ ሳሙ 28፡14
ዳን 2፡46
የሐዋ 16፡29
ራዕይ 3፡9

ጾም

1. በአፍ መጾም እንደሚገባ
ዕዝ 8፡21-23
ኤር 36፡9-10
ዘካ 8፡1d-20
ዮናስ 3፡5
ኢዮኤል 2፡12-15
የሐዋ 13፡2
2ኛ ቆሮ 6፡6

2. ከምግና ከቁጢ ከመብላት ጾም እንደሚገ
መዝ 108፡24
ዳን 9፡3
ዳን 10፡2-3
ሮሜ 14፡21

3. ጾም በብሉይ ኪዳን
ዘፀ 34፡28
ዘዳ 9፡9.18
መሳ 20፡26
1ኛ ሳሙ 7፡6
1ኛ ሳሙ 31፡13
2ኛ ሳሙ 1፡12-13
ዕዝራ 8፡21-23
ነህ 1፡4
አስቴር 4፡3, 16
መዝ 34፡13
መዝ 68፡10
መዝ 108፡24
ኢሳ 58፡3-12
ዳን 9፡3
ኢዩ 1፡14
ኢዩ 2፡12-15
ዮናስ 3፡5-8
ዘካ 7፡5
ዘካ 8፡18-20

4. ጾም በሐዲስ ኪዳን
ማቴ 4፡2
ማቴ 6፡16-18
ማቴ 9፡4
ማቴ 17፡21
ማር 2፡ 18
ሉቃ 2፡ 37
ሉቃ 18፡12
የሐዋ 13፡2,3
የሐዋ 14፡ 23
2ኛ ቆሮ 6፡6
2ኛ ቆሮ 11፡27

ሀ. ዐቢይ ጾም
ማቴ 4፡2

ለ. ረቡዕና ዐርብ
ማቴ 9፡15
ማቴ 26፡1

ሐ. የነነዌ ጾም
ዮናስ 3፡5

መ. የነቢያት ጾም
ዘዳግም 9፡9, 18
ዘፀ 34፡28
መዝ 34፡13

ሠ. የሐዋርያት ጾም
የሐዋ 13፡1-3
የሐዋ 14፡23
2ኛ ቆሮ 6፡6

..../

# ጥምቀት

1. ጥምቀት ከውሃና ከመንፈስ መወለድ ነው፡፡ ከውሃና ከመንፈስ ያልተወለደ ሰው አይድንም፡፡

ማር 16፡16 , ዮሐ 3፡5, 1ኛ ጴጥ 3፡21

2. ጥምቀት በዐደባ ሲለተጠነም

ሀ. ቅንናት

ዘሌ 12፡ 1-8
መዝ 8፡2
ኢሳ 49፡ 22
ማቴ 18፡ 1-6
ማቴ 19፡13-14
ማቴ 21፡16
ሉቃ 2፡21፡28
ሉቃ 10፡20-21

ለ. ገዢረኛ ጥምቀት

ዘፍ 17፡12
ዘፍ 17፡22-27
ዘፍ 21 ፡ 4
ዘሌዋ 12፡4
ሮሜ 2፡29
ቆላ 2፡11

ሐ. በአባቶች እምነት በቤተሰቡ ይጠመቁ ነበር

የሐዋ 2፡39
የሐዋ 16፡15
የሐዋ 16፡33-34

3. ጥምቀት በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም ነው
ማቴ 3፡16 , ማቴ 28፡19 , ሉቃ 3፡21-22
የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ
— ማር 16፡ 17-18
— የሐ.ሥ 3፡6
— 1ኛ ቆሮ 12፡ 4

ሀ. ተአምራት ማድረግ የሃይማኖት መመዘኛ ለሆን አይችልም :

ዘፀ 7፡11
ማቴ 7፡22-23
ማቴ 12፡38-39
ማቴ 16፡ 1-3
ማቴ 16፡ 17-18
ማቴ 24፡24
2ኛ ተሰ 2፡ 8-12
ራእይ 13፡13-14

ለ. በልሳን መናገር የሃይማኖት መመዘኛ ሊሆን አይችልም

የሐዋ 2፡1 - 13
1ኛ ቆሮ 12፡ 10
1ኛ ቆሮ 12፡30-31
1ኛ ቆሮ 13፡ 1-8
1ኛ ቆሮ 14፡5, 12

ቅዱስ ቁርባን /የጌታ ሥጋና ደም/

ኢሳ 19፡19
ማቴ 5፡23
ማቴ 26፡26-29
ሉቃ 22፡14-23
ዮሐ 6፡51-53
1ኛ ቆሮ 10፡ 14-21
1ኛ ቆሮ 11፡ 23 - 27
ዕብ 1[illegible]፡ 11-15

... /

## ክ ህ ነ ት

ማቴ 10፥ 1-3
ማቴ 16፥19
ማቴ 18፥18
ማቴ 28፥20
ሉቃ 24፥51
ዮሐ 20፥23

የሐዋ 1፥25
የሐዋ 6፥ 6
የሐዋ 13፥3
የሐዋ 14፥ 23
የሐዋ 20፥28
ፊልጵ 1፥ 1

1ኛ ጢሞ 3፥1-13
1ኛ ጢሞ 4፥14
1ኛ ጢሞ 5፥ 17 -22
2ኛ ዮሐ 1፥1, 2

## ን ስ ሐ

1. መፀፀት
   - ሕዝ 18፥30
   - ማቴ 4፥17
   - ማቴ 11፥20
   - ማቴ 21፥28-32
   - ሉቃ 13፥1-5
   - የሐዋ 26-20

2. መናዘዝ /ኑዛዜ/
   - ዘሌ 5፥5
   - ማቴ 3፥6
   - ማቴ 8፥4
   - የሐዋ 19፥18
   - 1ኛ ዮሐ 1፥9
   - ያዕ 5፥16

## ቅዱስ ጋብቻና ድንግልና

ሀ. ቅ/ጋብቻ
- ዘፍ 2፥24
- ማቴ 5፥32
- ማቴ 19፥4-6
- 1ኛ ቆሮ 7፥2
- ኤፌ 5፥28-32
- ዕብ 13፥4

ለ. ድንግልና
- ኢሳ 56፥ 3
- ማቴ 19፥10-12
- 1ኛ ቆሮ 7፥25-40

(1) [illegible]

በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ አሐዱ፡ አምላክ፡ አሜን!

## ቅዱሳን

ቅዱሳን፡ በሁለት፡ ይከፈላሉ። ይኸውም፦

1 ቅዱሳን፡ መላእክት፤

2 ቅዱሳን፡ ሰዎች፡ ናቸው።

"እኔ፡ እግዚአብሔር፡ አምላካችሁ፡ ቅዱስ፡ ነኝና፡ እናንተም፡ ቅዱሳን፡ ሁኑ።" ብሎ፡ መፍቀዱ፡ /ዘሌዋ. 11፥44-45፤ 19፥2/ ሰዎች፡ በመልካም፡ ሥራ፡ በሃይማኖት፡ ጸንተው፡ የእግዚአብሔር፡ ልጆች፡ እንዲሆኑ፡ መብት /ሥልጣን/፡ ተሰጥቶአቸዋል። /ዮሐ 1፥11-13/ ጌታችን፡ ከተከታዮቹ፡ ጋር፡ አንድነት፡ እንዳለው፡ በግንድና፡ በቅርንጫፍ፡ መስሎ፡ ለደቀመዛሙርቱ፡ ሲያስተምራቸው፤ "እኔ፡ የወይን፡ ግንድ፡ ነኝ፡ እናንተም፡ ቅርንጫፎች፡ ናችሁ።" ሲል፡ ተናግሯል። /ዮሐ 15፥5/ "ሥሩ፡ ቅዱስ፡ ከሆነ፡ ቅርንጫፎቹም፡ ደግሞ፡ ቅዱሳን፡ ናቸው። ሮሜ 11፥16 ቅዱሳን፡ መላእክትና፡ ጻድቃን፡ የጌታ፡ አገልጋዮች፡ ናቸውና፡ የእርሱ፡ ቅርንጫፎች፡ ናቸው።

### ሀ. ቅዱሳን፡ መላእክት፡ መቼ፡ ተፈጠሩ?

እግዚአብሔር፡ ሰማያትን፡ ሲፈጥር፡ አገልጋዮቹ፡ መላእክትንም፡ ፈጠረ። /ዘፍ 1፥1/ የተፈጠሩትም፡ በመጀመሪያው፡ ቀን፡ በዕለተ፡ እሑድ፡ ከእሳትና፡ ከነፋስ፡ ነው።

### ለ. የቅዱሳን፡ መላእክት፡ ቁጥር /ብዛት።/

የቅዱሳን፡ መላእክት፡ ብዛት፡ ወሰንም፡ ቁጥራቸው፡ አይታወቅም። ለአንድ፡ ጊዜ፡ ብቻ፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ ለአገልግሎት፡ የሚቆሙ፡ አእላፋት፡ /10 ሺህ፡ ጊዜ፡ 10 ሺህ/ እንደሆኑ፡ ነቢዩ፡ ዳንኤል፡ በራእይ፡ ተረድቷል። /ዳን 7፥10/ ብዛታቸውን፡ ከእግዚአብሔር፡ በስተቀር፡ ማንም፡ አያውቅም። የሰማይን፡ ሰራዊት፡ መቁጠር፡ ፈጽሞ፡ እንደማይቻል፡ ነቢዩ፡ ኤርምያስ፡ መስክሯል። /ኤር 33፥22/

## ሐ. የቅዱሳን፡ መላእክት፡ ተፈጥሮ፡

መላእክት፡ ማለት፡ የእግዚአብሔር፡ መልእክተኞች፡/የእግዚአብሔር፡ ተላላኪዎች/ ማለት፡ ነው። /መዝ 103/104 ቁ 4/ ከመጽሐፍ፡ ቅዱስ፡ ምንጭ፡ መሠረት፡ "መላእክቱን፡ መንፈስ፡ የሚያደርግ፡ አገልጋዮቹንም፡ የእሳት፡ ነበልባል፡ የሚያደርግ።" ተብሎ፡ መጻፉ። ሐዋርያው፡ ቅዱስ፡ ጳውሎስም፡ ቅዱሳን፡ መላእክት፡ መናፍስት/ረቂቃን/ እንደሆኑ፡ ያመለክታል። /ዕብ 1÷14/ ቅዱሳን፡ መላእክት፡ በረቂቅነታቸው፡ ከእሳትም፡ ከነፋስም፡ በላይ፡ ረቂቃን፡ መሆናቸውን፡ ያስገነዝበናል።

## መ. የመላእክት፡ ነገድ፡

የቅዱሳን፡ መላእክት፡ ነገድ፡ ዘጠና፡ ዘጠኝ፡ እንደሆነ፡ የቤተክርስቲያን፡ አባቶች፡ ያስተምሩናል። ይኸውም፡ ጌታ፡ ስለንስሐ፡ ሲያስተምር፡- "ለአንድ፡ ሰው፡ መቶ፡ በጎች፡ ቢኖሩት፡ ከእነርሱም፡ አንዱ፡ ቢባዝን /ቢጠፋ/፡ ዘጠናን፡ ዘጠኙን፡ በተራራ፡ ትቶ፡ የባዘነውን፡ አይፈልግምን? ቢያገኘው፤ እውነት፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ ካልባዘኑት፡ /ካልጠፉት/ ከዘጠና፡ ዘጠኙ፡ ይልቅ፡ በእርሱ፡ ደስ፡ ይለዋል። /ማቴ 18÷12/ የተናገረውን፡ መሠረት፡ በማድረግ፡ የጠፋው፡ በግ፡ ወይም፡ ጠፍቶ፡ የተገኘው፡ በግ፡ አዳም፡ ሲሆን፡ ያልጠፉት፡ ዘጠና፡ ዘጠኙ፡ በጎች፡ ያለው፡ ደግሞ፡ ዘጠና፡ ዘጠኙን፡ ነገድ፡ መላእክት፡ ማለቱ፡ እንደሆነ፡ ሊቃውንት፡ ያስተምሩናል። ቅዱስ፡ ያሬድም፡ ይህንን፡ መሠረት፡ በማድረግ፡ ስለጌታችን፡ በዮርዳኖስ፡ መጠመቅ፡ አስመልክቶ፡ ሲናገር፡ "ዘጠና፡ ዘጠኙን፡ ነገድ፡ ትቶ፡ በባሕር፡ መካከል፡ ቆመ፡ ብሏል።

## ሠ. የቅዱሳን፡ መላእክት፡ የነገድ፡ ቅደም፡ ተከተል፡፡

- ሱራፌል፡- ባለብዙ፡ ዓይኖች /ኢሳ 6÷2/
- ኪሩቤል፡- ባለብዙ፡ ክንፎች /ራእ 4÷6/
- መናብርት፡-
- ስልጣናት /ኃይላት/

- ስልጣናት /ገዦች/ /ቆላስያስ 1፥15/
- መኳንንት
- ቀደምት

ከነዚህ፡ ነገዶች፡ ውስጥ፡ በስም፡ የሚታወቁት፡ ሊቃነ፡መላእክት፡ በጣም፡ ጥቂቶች፡ ናቸው:: እነርሱም፡-

- ሚካኤል፡- ዳን 12፥1 ፤ ይሁዳ 1፥9 ፤ ራእ 12፥7
- ገብርኤል፡- ዳን 9፥21 ፤ ሉቃ 1፥19
- ሩፋኤል፡- ሄኖክ 10፥2-9 ፤ ጦቢት 12፥5
- ፋኑኤል፡- ሄኖክ 10፥2-9 ፤ ጦቢት 12፥5
- ኡራኤል፡- ዕዝራ፡ሱቱኤል 2፥1-4
- ራጉኤል፡- ጸሎተ፡ነገ
- ሳቁኤል፡- ››
- ሱራኤል /ሱርያል/ ››
- አፍኒን ››

ረ. የቅዱሳን፡ መላእክት፡ አገልግሎት

የቅዱሳን፡ መላእክት፡ አገልግሎት፡ በሁለት፡ ይከፈላል::

1 ያለእረፍት፡ እግዚአብሔርን፡ ማገልገል /ማመስገን/፡ መቀደስ::
/ኢሳ 6፥2 ፤ ራእ 4፥6-11 ፤ 5፥6-14/

2 ሰውን፡ ማገልገል፡ ነው:: ማለትም፡ ሰውን፡ መጠበቅ ፤ መርዳት ፤ ማገዝና፡ ማዳን፡ ነው::

ቅዱሳን፡ መላእክት፡ ከእግዚአብሔር፡ እየተላኩ፡ ሰውን፡ ለመርዳትና፡ ለማዳን፡ አገልግሎት፡ እንደሚፈጽሙ፡ መጽሐፍ፡ ቅዱስ፡ ያስረዳል::

የእግዚአብሔር፡ መልአክ፡ በከባድ፡ ችግር፡ ላይ፡ ወድቀው፡ የነበሩትን፡ እናትና፡ ልጅ፤ አጋርንና፡ እስማኤልን፡ ረዳቸው:: /ዘፍ 21፥15-20/:: ያዕቆብም፡- ከክፉ፡ ነገር፡ ያዳነው፡

የእግዚአብሔር፡ መልአክ፡ እንዲሆን፡ መስክሯል። /ዘፍ 48፥16/ ስለዚህ፡ ቅዱሳን፡ መላእክት፡ ማማለድ፡ ብቻ፡ ሳይሆን፡ የማዳን፡ ሥልጣን፡ አላቸው።

መናፍቃን፡ በድፍረት፡ መላእክት፡ ስለ፡ሰው፡ አይጸልዩም፡ ወደ፡ እግዚአብሔርም፡ አያማልዱም፡ ይላሉ። መጽሐፍ፡ ቅዱስ፡ ግን፡ ቅዱሳን፡ መላእክት፡ ከማማለድም፡ አልፈው፡ ሰውን፡ ማዳን፡ እንደሚችሉ፡ ይመሰክራል።

"የእግዚአብሔር፡ መልአክ፡ በሚፈሩት፡ ሰዎች፡ ዙሪያ፡ ይሰፍራል፡ ያድናቸውማል።" ሲል፡ መጽሐፍ፡ ቅዱስ፡ ይመሰክራል። /መዝ 33፥7/ ከክፉ፡ ነገር፡ ሁሉ፡ ያዳነኝ፡ የእግዚአብሔር፡ መልአክ፡ ነው፡ ብሎ፡ ያዕቆብ፡ የተናገረውም፡ በዚሁ፡ መሠረት፡ ነው። /ዘፍ 48፥16/

እግዚአብሔር፡ አምላክ፡ ወዳጆቹን፡ የሚረዳው፡ ወይም፡ የሚያድነው፡ በቅዱሳን፡ መላእክት፡ እያደረ፡ ወይም፡ ቅዱሳን፡ መላእክትን፡ እየላከ፡ ነው። ለማስረጃ፡ ያህል፡ <u>የሦስቱ፡ ወጣቶችን</u>፡ /የሠለስቱ፡ ደቂቅን/ ታሪክና፡ <u>የዳንኤልን</u>፡ ታሪክ፡ እንመልከት። /ዳን 3፥24-30/ ፤ 6፥22-23/ <u>ቅዱስ፡ ጴጥሮስንም</u>፡ ከእስር፡ ቤት፡ ጐትቶ፡ ያወጣውና፡ ከሞት፡ ያዳነው፡ የእግዚአብሔር፡ መልአክ፡ ነው። /ሐዋ 12፥1/

<u>ሐ. ቅዱሳን፡ መላእክት፡ የእግዚአብሔር፡ እንደራሴዎች፡ ናቸው።</u>

እንደራሴ፡ ማለት፡ እንደዋናው፡ ሆኖ፡ የሚሠራ፡ ሙሉ፡ ሥልጣን፡ ያለው፡ ማለት፡ ነው። ስለዚህ፡ ቅዱሳን፡ መላእክት፡ እንደ፡ እግዚአብሔር፡ ሆነው፡ ሰውን፡ እንዲረዱና፡ እንዲታደጉ፡ ከእግዚአብሔር፡ የተሾሙ፡ የእግዚአብሔር፡ እንደራሴዎች፡ ናቸው።

እስራኤላውያንን፡ ከፈርዖን፡ እጅ፡ አድኖ፡ በበረሃ፡ ይመራ፡የነበረው፡ መልአክ፡ ነበር።

"በመንገድህ፡ ይጠብቅህ፡ ዘንድ፡ ወዳዘጋጀሁትም፡ ሥፍራ፡ ያገባህ፡

ስለሌለው፡ ይጸልይ፡፡ የጻድቅ፡ ሰው፡ ጸሎት፡ በሥራዋ፡ እጅግ፡ ኃይል፡ ታደርጋለች፡፡ ኤልያስ፡ እንደኛው፡ ሰው፡ ነበር፡፡ ዝናም፡ እንዳይዘንም፡ ጸለየ፡ ሰማይም፡ ዝናምን፡ ሰጠ፡ ምድሪቱም፡ ፍሬዋን፡ አበቀለች፡፡ /ያዕ 5÷13-18/

## በአዲስ፡ ኪዳን፡ አማላጅነት

ለመሆኑ፡ በዮሐ 14÷6 የሚለው፡ ምንድነው? እውነት፡ ጌታ፡ አማላጅ፡ ወይስ፡ ተማላጅ?

ቢገባን፡ አማላጅ፡ ነው፡ ባዮች፡ ተሳስተዋል፡፡ ይህ፡ ሁሉ፡ ኑፋቄ፡ ቅዱሳንን፡ ተራ፡ ሰው፡ አድርገው፡ ለማቅረብ፡ የሚሞክሩና፡ የዲያቢሎስን፡ ገንዘብ፡ የሆነውን፡ ትዕቢት፡ የተሸከመው፡ ናቸው፡፡ በቀጥታ፡ እንጠይቃለን፡ እንቀርባለን፡ ይላሉ፡፡ እኛ፡ ግን፡ ከመጽሐፍ፡ ቅዱስ፡ በተማርነውና፡ ቃሉን፡ ለመፈፀም፡ በቀጥታ፡ ወደ፡ ጌታ፡ ቤት፡ ለመቅረብ፡ ብቁ፡ አይደለሁም፡ በኃጢያት፡ ባሕር፡ የምዋኝ፡ ነኝ፡ ብለን፡ እግዚአብሔር፡ ባከበራቸው፡ መላእክትና፡ ቅዱሳን፡ አማካኝነት፡ መጸለይ፡ ትህትናን፡ ወንድማዊ፡ ፍቅርን፡ ያመለክታል፡፡

"በእኔ፡ በቀር፡ ወደ፡ አብ፡ የሚመጣ፡ የለም" ማለት፡ እኔን (በእኔ፡ የባሕርይ፡ አምላክነት) ያላመኑ፡ አብን፡ ሊያምን፡ አይችሉም፡፡ አብም፡ ሊቀበለው፡ አይችልም፡ ማለት፡ ነው፡ እንጂ፡ ቅዱሳን፡ ሊያማልዱ፡ አይችሉም፡ ለማለት፡ አይደለም፡፡

በመሠረቱ፡ ጌታ፡ "እኔ፡ ሕግንና፡ ነቢያትን፡ ለመሻር፡ የመጣሁ፡ አይምሰላችሁ፡፡ ልፈፅም፡ እንጂ፡ ለመሻር፡ አልመጣሁምና፡፡" /ማቴ 5÷17-20/ የባሕርይ፡ አምላክ፡ ተማላጅ፡ አምላክ፡ ነው፡ ማማለድ፡ ለፍጡር፡ እንጂ፡ ለፈጣሪ፡ አይደለም፡፡

ሀ. እናንተን፡ የሚቀበል፡ እኔን፡ ይቀበላል፡፡ ነቢይን፡ በነቢይ፡ ስም፡ የሚቀበል፡ የነቢይን፡ ዋጋ፡ ይወስዳል፡፡ ጻድቅን፡ በጻድቅ፡ ስም፡ የሚቀበል፡ የጻድቅን፡ ዋጋ፡ ይወስዳል፡፡ ማንም፡ ከእነዚህ፡

ከታናናሾቹ፡ ለአንዱ፡ ቀዝቃዛ፡ ጽዋ፡ ውሃ፡ ብቻ፡ በደቀ መዝሙር፡
ስም፡ የሚያጠጣ፡ እውነት፡ እላችኋለሁ፡ ዋጋው፡ አይጠፋበትም።"
/ማቴ 10÷40-42/

ለ <u>ያዕ 5÷14-19</u> የቅዱሳን፡ ጸሎት፡ በሥራዋ፡ እጅግ፡ ታላቅ፡ ኃይል፡
እንደምታደርግ፡ ይገልፃል። እንደሁም፡ የካህናት፡ ጸሎት /አማላጅነት/
ከሥጋ፡ ደዌና፡ ከኃጢያት፡ ደዌ፡ እንደሚፈውስ፡ ይገልፃል።

ሐ የማቴዎስ፡ 15÷21-28 የሐዋርያትን፡ አማላጅነት፡ ያሳያል።

<u>መዝ 88(89)÷3</u>፡ "ከመረጥሁት፡ ጋር፡ ቃል፡ኪዳኔን፡ አደረግሁ፡"
ይላል። እግዚአብሔር፡ ለወዳጆቹ፡ የገባውን፡ ቃል፡ኪዳን፡ እንደማያፈርስ፡
ያስረዳል። አልፎም፡ ቅዱሳን፡ የፀጋ፡ አምላክነት፡ ይገባቸዋል።

<u>ዘፀ 7÷1</u> "እግዚአብሔር፡ ሙሴን፡ ለፈርዖን፡ አምላክ፡ አደርግሃለሁ፡
ወንድምህም፡ አሮን፡ ነቢይ፡ ይሆንልሃል።"

<u>መዝ 81(82)÷1-8</u> "እኔ፡ አማልክት፡ ናችሁ፡ አልሁ" ብሎ፡
የተናገረው፡ስለቅዱሳን፡ አይደለምን?

<u>2ኛ ቆሮ 5÷20</u> "እኛ፡ በክርስቶስ፡ ፈንታ፡ ክርስቶስን፡ መስለን፡
እንለምናለን ።

ቅዱሳን፡ ከማማለድ፡ አልፈው፡ ይፈርዳሉ። የሚሳናቸው፡ ነገር፡
የለም። /ማቴ 17÷19/ "የሰናፍጭ፡ ቅንጣት፡ ታህል፡ እምነት፡
ቢኖራችሁ፡ ይህን፡ ተራራ፡ ከዚህ፡ ወደዚያ፡ እለፍ፡ ብትሉት፡ ያልፋል።
የሚሳናችሁ፡ ነገር፡ የለም።"

<u>ማቴ 5÷14</u> "እኔ፡ የዓለም፡ ብርሃን፡ ነኝ።" ብሏል። በዮሐ ፰÷12
ለሐዋርያት፡ ደግሞ፡ "የዓለም፡ ብርሃን፡ ናችሁ" ብሏል።" ታዲያ፡
አማልደው፡ ከጌታ፡ ጋር፡ካላገናኙን፡ ምኑን፡ ብርሃን፡ ሆኑት?

<u>ጻድቃን፡ ከሞቱ፡ በኋላ</u>።

"በሰማይ፡ እግዚአብሔርን፡ እንደሚያገለግሉ፡ መላእክት፡ ይሆናሉ፡
ብሏል፡ ጌታ። <u>ማቴ 22÷27-30</u>.

ራእ 6÷9-11 ስለሞቱት፡ ሰዎች፡ ነፍስ፡ አየሁ፡ (ስለእግዚአብሔር፡ ቃል፡ ስለሞቱት፡ ሰማዕታት) እውነተኛ፡ የባሕርይ፡ አምላክ፡ አቤቱ፡ ደማችንን፡ በግፍ፡ ያፈሰሱትን፡ ሰዎች፡ አትበቀላቸውም፡ ብለው፡ ጠየቁት። ገና፡ በሰማዕትነት፡ የሚሞቱ፡ ብዙ፡ አሉና፡ አላቸው። ይህ፡ የሚያሳየው፡ ከሞት፡ በኋላ፡ መጸለየን፡ አይደለምን?

ማር 12÷26 "እኔ፥ የሕያዋን፡ የእነአብርሃም፡ የነይስሐቅ፡ አምላክ፡ ነኝ፡ እንጂ፡ የሙታን፡ አምላክ፡ አይደለሁም።" አብርሃም፥ ይስሐቅ፡ ከሞቱ፡ በኋላ፡ አይደል፡ እንዴ፡ ስለአብርሃም፡ ስለይስሐቅ፡ ብለህ፡ እያሉ፡ እነሙሴ፡ ይለምኑት፡ የነበረው? በሠናት፡ ጽድቅ፡ ሥራ፡ ህያዋን፡ እንጂ፡ ሙታን፡ አለመሆናቸውን፡ ገለፀ።

ሉቃ 16÷19-31 ሃብታሙ፡ ስለአብርሃም፡ ማረኝ፡ ማለቱ፡ ቅዱሳን፡ ለማማለድ፡ ብቻ፡ ሳይሆን፡ ይፈርዳሉም።

"እውነት፡ እላችኋለሁ፡ እናንተስ፡ የተከተላችሁኝ፡ በዳግመኛ፡ ልደት፡ የሰው፡ ልጅ፡ በክብሩ፡ ዙፋን፡ በሚቀመጥበት፡ ጊዜ፡ እናንተ፡ ደግሞ፡ በአስራ፡ሁለቱ፡ የእስራኤል፡ ነገድ፡ ልትፈርዱ፡ በአስራሁለት፡ ዙፋን፡ ትቀመጣላችሁ።" /ማቴ 19÷28-29/

ቅዱስ፡ ጳውሎስ፡ በ1ኛ ቆሮ 6÷2 "ቅዱሳን፡ በዓለም፡ ላይ፡ እንዲፈርዱ፡ አታውቁምን?" ይለናል።

አፉን፡ ከፍቶ፡ ሊውጠን፡ ከሚንቆረጠጠው፡ ዲያብሎስ፥ ሠራዊቶቹን፡ አሰማርቶ፡ ከአንዲቱ፡ ሃይማኖት፡ ሊያስወጣን፡ ስለሚፈልግ፡ ቅዱሳን፡ ከጐናችን፡ ሆናችሁ፡ ምሩን፡ ጸልዩልን፡ እንላለን፡

አሜን!

"ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር"

በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ አሐዱ፡ አምላክ፡ አሜን!

<u>ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ አማላጅ፡ ወይስ፡ ተማላጅ?</u>

አማላጅ፡ ስንል፡ በውስጡ፡ ያዘለው፡ ማን? ፣ ለማን፣ ወደማን? የሚሉትን፡ ጥያቄዎች፡ ያስነሳል።

ስለአማላጅ፡ ሦስት፡ ነገሮች፡ ተምረናል።

1ኛ. የሚማለድለት ፣

2ኛ. የሚማልድ /አማላጅ/ ፣

3ኛ. ምልጃን፡ ተቀብሎ፡ ምህረትን፡ የሚሰጥ፡ /ተማላጅ/

በተራ፡ ቁጥር፡ ሦስት፡ የተጠቀሰው፡ አምላክ፡ እንደሆነ፣ ይህም፡ አምላክ፡ መድኃኒታችን፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ እንደሆነ፡ የታወቀ፡ ነው። ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ አምላክ፡ ተማላጅ፡ እንጂ፣ አማላጅ፡ ፍጡር፡ አይደለም።

1 <u>የክርስቶስ፡ አምላክነት፡-</u> <u>ማቴ 8፥25</u> ደቀመዛሙርቱ፡ አድነን፡ ጠፋን፡ እንዳሉት፣ "እርሱም፡ ተነስቶ፡ ነፋሱንና፡ ባሕሩን፡ ገሠጸ፡ ታላቅ፡ ፀጥታም፡ ሆነ።

<u>ማቴ 9፥20</u> 12 ዓመት፡ ደም፡ ሲፈሳት፡ የነበረችውን፡ ሴት፡ እንዳዳነ።

<u>ማቴ 9፥18</u> የመኰንኑን፡ ልጅ፡ ከሞት፡ እንዳስነሳ

<u>ማቴ 20፥29</u> ሁለት፡ ዕውሮች፡ ቀርበው፡ "ዓይናችንን፡ ይከፈቱ፡ ዘንድ" እንሻለን፡ እንዳሉት፣ እርሱም፡ እንደፈቃዳቸው፡ ዓይናቸውን፡ እንዳበራ።

<u>1ኛ ጢሞ 1፥17</u> " <u>ብቻውን፡ አምላክ፡ ለሚሆን</u>፡ ለማይጠፋው፡ ለማይታየውም፡ ለዘመናት፡ ንጉሥ፡ ምስጋናና፡ ክብር፡ እስከ፡ ዘላለም፡ ድረስ፡ ይሁን፡ አሜን።"

<u>ቲቶ 2፥11-14</u> "ሰዎችን፡ ሁሉ፡ የሚያድን፡ የእግዚአብሔር፡ ጸጋ፡ ተገልጦአልና፣ ይህም፡ ጸጋ፡ ኃጢያተኛነትንና፡ ዓለማዊ፡ ምኞትን፡ ክደን÷ የተገለጠውን፡ ተስፋችንን፡ እርሱም፡ <u>የታላቁን፡ የአምላካችንን፡ የመድኃኒታችንን፡ የኢየሱስን፡ ክብር</u>፡ መገለጥ፡ እየጠበቅን፣ ራሳችንን፡ በመግዛትና

በጽድቅ: እግዚአብሔርንም: በመምሰል: በአሁኑ: ዘመን: እንድንኖር: ያስተምረናል::"

ሆሴዕ 13፥4 "እኔ: ግን: ከግብጽ: ምድር: ጀምሬ: አምላክህ: እግዚአብሔር: ነኝ፤ ከእኔም: በቀር: ሌላ: አምላክ: አታውቅም:: ከእኔም: በቀር: ሌላ: መድኃኒት: የለም::"

1ኛ ዮሐ 5፥20-22 "የእግዚአብሔርም: ልጅ: እንደመጣ: እውነተኛውም: የሆነውን: እናውቅ: ዘንድ: ልቡናን: እንደሰጠን: እናውቃለን:: እውነተኛውም: በሆነው: በእርሱ: አለን፥ እርሱም: ልጁ: ኢየሱስ: ክርስቶስ: ነው:: እርሱ: እውነተኛ: አምላክና: የዘላለም: ሕይወት: ነው:: ልጆች: ሆይ: ከጣዖታት: ራሳችሁን: ጠብቁ::"

ሮሜ 9፥5 "ከእነርሱም: ክርስቶስ: በሥጋ: መጣ:: እርሱም: ከሁሉ: በላይ: ሆኖ: ለዘላለም: የተባረከ: አምላክ: ነው፤ አሜን::"

ዮሐ 1፥1 "በመጀመሪያው: ቃል: ነበረ:: ቃልም: በእግዚአብሔር: ዘንድ: ነበረ:: ቃልም: እግዚአብሔር: ነበረ::"

ዮሐ 11፥25 "እኔ: ትንሣኤና: ሕይወት: ነኝ:: የሚያምንብኝ: ቢሞት: እንኳን: ሕያው: ይሆናል::"

ዮሐ 10፥30 "እኔና: አብ: አንድ: ነን::"

ዮሐ 14፥8 ፊልጶስ: ጌታን: "አብን: አሳየንና: ይበቃናል::" ባለው: ጊዜ፥ ከአብ: ጋር: በህልውና: አንድ: መሆኑን: ሲገልጽ፥ "ይህን: ያህል: ዘመን: ከእናንተ: ጋር: ስኖር: አታውቀኝምን? እኔን: ያየ: አብን: አይቷል፤ እንዴት: አንተ:- አብን: አሳየን: ትላለህ? እኔ: በአብ: እንዳለሁ: አብን: በእኔ: እንዳለ: አታምንምን?"

በዮሐ 10፥38 ላይም: ይህንኑ: ቃል: በድጋሚ: "አብ: በእኔ: እንደሆነ: እኔም: በአብ: እንደሆንሁ:" በማለት: በህልውና: ከአብ: ጋር: አንድ: እንደሆነ: ገልጾታል::

2 ክርስቶስ፡ እግዚአብሔር፡ ነው።

የሐዋ 1፥11 "ይህ፡ ከእናንተ፡ ወደ፡ ሰማይ፡ የወጣው፡ ኢየሱስ፡ ወደ፡ ሰማይ፡ ሲሄድ፡ እንዳያችሁት፥ እንዲሁ፡ ይመጣል።"

ልበ፡ አምላክ፡ ዳዊትም፡ የኢየሱስ፡ ክርስቶስን፡ ዳግም፡ ምጽአት፡ ሲናገር፡ በመዝሙር 49(50)፥2 ላይ፡ "ከክብሩ፡ ውበት፡ ከጽዮን፡ እግዚአብሔር፡ በግልጽ፡ ሆኖ፡ ይመጣል።" ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ እግዚአብሔር፡ መሆኑን፡ ዳዊት፡ ስላወቀ፥ ክርስቶስን፡ እግዚአብሔር፡ ብሎ፡ እንደጠራው፡ ታስተውላለህን?

ዘካ 14፥5 "አምላኬ፡ እግዚአብሔር፡ ከቅዱሳኑ፡ ሁሉ፡ ጋር፡ ይመጣል።"

1ኛ ተሰ 3፥12 "ጌታችንም፡ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ከቅዱሳኑ፡ ሁሉ፡ ጋር፡ ሲመጣ"

የሐዋ 1፥9 ስለጌታችን፡ ዕርገት፡ እንዲህ፡ ያስነብበናል። "ይህንን፡ ከተናገረ፡ በኋላ፡ እነርሱ፡ እያዩት፡ ከፍ፡ ከፍ፡ አለ፥ ደመናም፡ ከዓይናቸው፡ ሰውሮ፡ ተቀበለችው።" ልበ፡ አምላክ፡ ዳዊትም፡ በመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ተቃኝቶ፡ ስለ፡ ጌታችን፡ ዕርገት፡ እንዲህ፡ ሲል፡ በትንቢት፡ ዘመረ።

በመዝ 46(47)፥5 ላይ "አምላክ፡ በእልልታ፤ እግዚአብሔር፡ በመለከት፡ ድምጽ፡ ዐረገ።" አሁንም፡ ክርስቶስን፡ እግዚአብሔር፡ ብሎ፡ እንደጠራው፡ ልብ፡ በል።

የሐዋ 20፥28 "እግዚአብሔር፡ በደሙ፡ የዋጃትን፡ ቤተክርስቲያን..." ለእግዚአብሔር፡ ምን፡ ደም፡ አለው። በእውነቱ፡ ይህ፡ ቃል፡ የሚናገረው፡ ከድንግል፡ ማርያም፡ ከሥጋ፡ ሥጋ፡ ከነፍሷ፡ ነፍስ፡ ስለነሣው፡ ስለ፡ ጌታችንና፡ አምላካችን፡ ስለ ኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ አይደለምን?

ኢሳ 45፥20 "እኔ፡ ጻድቅ፡ አምላክና፡ መድኃኒት፡ ነኝ።"

በሆሴ 13፥4 ላይም፡ እግዚአብሔር፡ መድኃኒት፡ እንደሆነ፡ ተገልጿል።

ቲቶ 1፥3 "መድኃኒታችንም፡ እግዚአብሔር፡ እንዳዘዘ..." ይላና፡

ዮሐ 6፥47 "በእኔ፡ የሚያምን፡ የዘላለም፡ ሕይወት፡ አለው።
ማር 16፥16 "ያመነ፡ የተጠመቀ፡ ይድናል።"
ሐዋ 8፥36 ጃንደረባው፡ በእምነት፡ ለመዳን፡ እንደተጠመቀ።
1ኛ ዮሐ 2፥2-3 እኛን፡ አብነት፡ ያደረገ፡/ትዕዛዛን፡የጠበቀ/ ክፍድ፡
ይድናል።
ዮሐ 14፥6 "እየሱስም፡ እኔ፡ መንገድና፡ እውነት፡ ሕይወትም፡ ነኝ።
በእኔ፡ በቀር፡ ወደ አብ፡ የሚመጣ፡ የለም።"

በዚህ፡ ጥቅስ፡ የሚያነካክሱ፡ ክፍሎች፡ አሉ። በመሠረቱ፡ ይህ፡ ምዕራፍ፡ የሚያስተምረው፡ ስለ ሰማያት፡ ነው። በየቁጥሩ፡ እየተነተንን፡ እንመለከታለን።

ቁ 1. አርእስቱ፡ በሰማያት፡ ላይ፡ ይመሠረትና፡ ስለ፡ እምነት፡ ያስረዳል።

ቁ.5 የመንግስተ፡ ሰማያትን፡ ጉዳና (መንገዱን) ታውቃላችሁን? ቢላቸው፡ መንገዱን፡ እንዴት፡ እናውቃለን፡ ቢሉ፡ መንገዱ፡ በክርስቶስ፡ ማመን፡ መሆኑን፡ ያገለፃል።

ቁ.6 ወደ፡ አብ፡ የምወስዳችሁ፡ መንገድ፡ እኔ፡ ነኝ፡ ይላቸዋል፡ እንጂ፡ አማላጅ፡ ነኝ፡ አላለም።

ቁ.7 "እኔንስ፡ ብታውቁኝ፡ አባቴንም፡ ደግሞ፡ ባወቃችሁ፡ ነበር። ከአሁን፡ ጀምሮ፡ ታውቁታላችሁ፡ አይታችሁትማል።" በማለት፡ መንገድ፡ ያለውን፡ የሰማያት፡ ዕውቀት፡ መሆኑን፡ ተርጉሞ፡ ወልድ[illegible]ን፡ በሰማያት፡ ማወቅ፡ አብንም፡ በሰማያት፡ ማወቅ፡ መሆኑን፡ ያስረዳቸዋል።

ቁ 8-11 አብ፡ በወልድ፡ ወልድም፡ በአብ፡ ህልው፡ መሆኑን፡ ያገለፃል። በአጠቃላይ፡ ስለ ምሥጢረ፡ ሥላሴ፡ የአንድነትን፡ የሦስትነትን፡ ነገር፡ ይመሰክራል።

ተመሳሳይ፡ ጥቅሶች፦

2ኛ ቆሮ 8፥9 ፡ ዮሐ 17፥1 ፡ ዕብ 7፥11 ፡ ሮሜ 5፥12

ሀገር 2÷1 ፤ የሐዋ 9÷3-5 ፤ የሐዋ 2÷21 ፤ ሮሜ 10÷8-13፤
ዕብ 1÷5-14 ፤ 1ኛ ተሰ 4÷16 ፤ ራእ 12÷1 ፤ ማርቆ 5÷21-43
የሐዋ 9÷36።

የቅዱሳንን፡ ጸሎት፡ የምዕመናንን፡ ትህትና፡ ተመልክቶ፡ በእናቱ፡ በቅድስት፡ ድንግል፡ ማርያም፡ አማላጅነት፡ ይቅር፡ ይበለን።

"ወስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር"

"ባለቤቱን፡ ካልናቁ፡ አጥሩን፡ አይነቀንቁ" እንዲሉ፡ የጌታችንን፡ አገልጋዮችን፡ ማለትም፡ ቅርንጫፎቹን፡ ማክበር፡ ስንችል፡ ነው፡ የጌታን፡ ትእዛዛት፡ መጠበቅ፡ የምንችለው። "ብትወዱኝስ ፡ ትእዛዛቴን፡ ጠብቁ ፡" ነው፡ ያለው፡ ጌታችንና፡ መድኃኒታችን፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዮሐ 7÷21

በስመ፡ አብ፡ ወወልድ፡ ወመንፈስ፡ ቅዱስ፡ አሐዱ፡ አምላክ፡ አሜን!

## መዝሙር

መዝሙር፡ ምንድን፡ ነው?

መዝሙር፡ የባሕርይ፡ አምላክ፡ ለሆነ፡ እግዚአብሔር፡ በሰማይና፡ በምድር፡ የሚመሰገንበት፡ አቢይ፡ የጸሎት፡ ክፍል፡ የሆነ፡ ጣዕመ፡ ዜማ፡ ነው። "እግዚአብሔርን፡ አመስግኑ፥ መዝሙር፡ መልካም፡ ነውና።"
መዝ 146፥1 ፤ ዘፀ 15፥1-22 ፤ ኢሳ 6፥1-5 ፤ ራእ
መዝ 65፥1-5

መዝሙር፡ ማለት፥ ዘመረ፡ አመሰገነ፡ ከሚለው፡ የግዕዝ፡ ቃል፡ የወጣ፡ ሲሆን፥ ቀጥተኛ፡ ትርጉሙም፡ ምስጋና ፤ ልመና ፤ መማጸን ፤ ማሬሬት ፤ ማስደሰት ፤ መደሰትና፡ ማዜም፡ ማለት፡ ነው።
"ኑ፡ በእግዚአብሔር፡ ደስ፡ ይበለን።

መዝ 149፥1 ፤ መዝ 150፥7-17 ፤ መዝ 80፥1-13 ፤ ማቴ 26፥30
ማር 14፥26 ፤ የሐዋ 16፥25 ፤ ቆላ 3፥16-25 ፤ ራእ 14፥1-4 ፤
ራእ 15፥2-4 ፤ ማቴ 21፥9 ፤ ማር 11፥9 ፤ ሉቃ 19፥36

ዜማ፡ በቀጥታ፡ ሲፈታ፡ ጩኸት /ድምጽ/ ማሰማት፡ ማለት፡ ነው። ይሁን፡ እንጂ፤ ዜማ፡ የምስጋና፡ ብቻ፡ ሳይሆን፡ የሐዘን ፤ የለቅሶ ፤ የቀረርቶ ፤ የሽለላ ፤ የፉከራና፡ የደስታ ፤ የስሜት፡ ሁሉ፡ መግለጫ፡ ድምጽ፡ ነው። ኢሳ 6፥1-5 ፤ ማቴ 26፥30

እዚህ፡ ላይ፡ ግን፥ ዜማ፡ ባልን፡ ጊዜ፡ የምስጋና፡ መዝሙር ፤ ድምጽ ፤ ሐሴት፡ ማለታችን፡ ነው።

የመዝሙር፡ ወይም፡ የዜማ፡ ጥቅሙ፡ ምንድን፡ ነው?

ሀ. እግዚአብሔርን፡ በተመስጦ፡ ለማመስገን፡ ለመቀደስ
ለ. ወደ፡ እግዚአብሔር፡ ልባዊ፡ ጸሎትን፡ ወይም፡ ልመናን፡ በማሬሬት፡ ለማቅረብ።
ሐ. መዝሙር፡ ለመማሪያና፡ ለማስተማሪያ፡ ወይም፡ ልብን፡ ለማነጽና፡ ነፍስን፡ ለማስደሰት፥ ማለት፡ መንፈስን፡ ለማደስ፡ ለምክር፡ ለተግሣጽና፡ ለመጽናናት፡ እጅግ፡ ይጠቅማል።

ይኸውም፡ በዕብራውያን፡ ዘንድ፡ ሰባት፡ ማለት፡ ፍፁም፡ ሙሉ፡ ማለት፡ ነው። ሥጋ፡ ወደሙ፡ የሚቀበሉ፡ ሰዎችም፡ በሃይማኖትና፡ በምግባር፡ ፍፁማን፡ ሆነው፡ መቀበል፡ እንደሚገባቸው፡ ለማስረዳት፡ ነው።

ሐ. እስከ፡ ሦስት፡ ሆነው፡ ሲቀድሱ፡ በጎታና፡ በእስከ፡ ሁለቱ፡ ሐዋርያት፡ ምሳሌ፡ ነው።

መ. ሃያ፡ አራት፡ ሆነው፡ ሲቀድሱ፡ በሃያ፡ አራቱ፡ ካህናተ፡ ሰማይ፡ ምሳሌ፡ ነው።

8 በቅዳሴ፡ ጊዜ፡ "እግዚኦ" ሲባል፡ ለኃይለ፡ ቃሉ፡ መግለጫ፡ ሆኖ ፲፪ /አስራ ሁለት/ ጊዜ፡ የደወል፡ ድምፅ፡ ይሰማል። ይኸውም፡ የአስራ፡ ሁለቱ፡ ሐዋርያት፡ ስብከት፡ ምሳሌ፡ ሆኖ፡ የድምፅ፡ አንድ፡ ዓይነት፡ መሆኑም፡ ሁሉም፡ የአንድ፡ ጌታችን፡ ቃል /ወንጌል/ ለማስተማራቸው፡ ምሳሌ፡ ነው።

9 ድርገት፡ ሲወርድ፡ ሰባት /፯/ ጊዜ፡ የደወል፡ ድምፅ፡ ይሰማል። ይኸውም፡ የሰባቱ፡ ምሥጢራተ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ምሳሌ፡ ነው።

10 በቅዳሴ፡ ጊዜ፡ ለሙካኑ፡ የሚለብሱት፡ ልብስ፡ ለብሰ፡ ተክህና፡ ይባላል። የመንፈሳዊ፡ አገልግሎት፡ ልብስ፡ ማለት፡ ነው።

ከ 1-10 ተራ፡ ቁጥር፡ የተዘረዘረው፡ በጸሎት፡ ቅዳሴ፡ ጊዜ፡ ለሚከናወነው፡ ሁኔታና፡ ነዋየ፡ ቅድሳት፡ ምሥጢር፡ ነው።

## ማኅሌት

ማኅሌት፡ ማለት፡ "ኀለየ" ማለት፡ ዜመ፤ ዘመረ፤ አመሰገነ፡ ከሚለው፡ የግዕዝ፡ ቃል፡ የወጣ፡ ሲሆን፡ የምስጋና፡ መዝሙርን፡ ለእግዚአብሔር፡ ማቅረብ፡ ማለት፡ ነው።

1 መቃኛት
2 መቀበል
3 መዓሪት
4 መመሪት
5 ዝማሜ
6 ቁም /ንዑስ፡ መረግድ/ በወርኃ፡ ጾም፡ ሽብሸባ
7 አቢይ፡ መረግድ
8 ጽፋት /ከአመላለስ/ መለስ፡ ወረብ፡ ጋር
9 ጽርብ፡ ጽፋት
10 የጥብጨባ፡ ጽፋት።

ወስብሐት፡ ለእግዚአብሔር

እንዲሁም፡ የሰማዕታትን፡ እውነተኛነት፡ በአምላካዊ፡ ቃል፡ እናረጋግጣለን።

ንስሐ

ሉቃ 12፥40 "እናንተ፡ ደግሞ፡ ተዘጋጅታችሁ፡ ኑሩ፤ የሰው፡ ልጅ፡ በማታስቡበት፡ ሰዓት፡ ይመጣልና።"

ሬቃችን፡ ሣጠዩቃችንን፡ ለንስሐት፡ መዘጋጀት፡ እንዳለብን፡ (ሰርክ) መማገት፡ እንዳለብን፡ ሲያስረዳን፡ እሥር፡ ለምጻሞችን፡ ከፈወሳቸው፡ በኋላ፡ "ሂዱና፡ ራሳችሁን፡ ለካህናት፡ አሳዩ" ማለትም፡ የሠራችሁትን፡ ኃጢአት፡ ለካህናት፡ አሳውቁ፡ በማለት፡ ተናግሯል። ሉቃ 17፥11-15

ማር 13፥33 "ጊዜው፡ መቼ፡ እንደሆነ፡ አታውቁምና፡ ተጠንቀቁ፡ ትጉ፡ ጸልዩም።"

ሞት

ሮሜ 6፥23 "የኃጢአት፡ ደመወዝ፡ ሞት፡ ነውና።"

ሮሜ 8፥6 "ስለ፡ ሥጋ፡ ማሰብ፡ ሞት፡ ነውና፤ ስለ፡ መንፈስ፡ ማሰብ፡ ግን፡ ሕይወትና፡ ሰላም፡ ነው።"

ሮሜ 8፥13 "እንደሥጋ፡ ፈቃድ፡ ብትኖሩ፡ ትሞቱ፡ ዘንድ፡ አላችሁና።"

ዮሐ 8፥21 "እኔ፡ እሄዳለሁ፡ ትፈልጉኛላችሁም፡ በኃጢአታችሁም፡ ትሞታላችሁ። እኔ፡ ወደምሄድበት፡ እናንተ፡ ልትመጡ፡ አትችሉም፡ አላቸው።"

ማቴ 8፥21 "ተከተለኝ፡ ሙታናቸውን፡ እንዲቀብሩ፡ ሙታንን፡ ተዋቸው፡ አለው።"

1ዮሐ 5፥16 "ማንም፡ ወንድሙን፡ ሞት፡ የማያገባውን፡ ኃጢአት፡ ሲያደርግ፡ ቢያየው፡ ይለምን። ሞትን፡ የማያገባውን፡ ኃጢአት፡ ላደረጉት፡ ሕይወትን፡ ይሰጣቸዋል። ሞት፡ የሚያገባ፡ ኃጢአት፡ አለ። ስለዚያ፡ እንዲጠይቅ፡ አልልም። ዓመፃ፡ ሁሉ፡ ኃጢአት፡ ነው። ሞትም፡ የማያገባ፡ ኃጢአት፡ አለ።"

ኤፌ 2፥1 "በበደላችሁና፡ በኃጢአታችሁ፡ ሙታን፡ ነበራችሁ።"

1ጴጥ 2፥11 "ወዳጆች፡ ሆይ፤ ነፍስን፡ ከሚዋጋ፡ ሥጋዊ፡ ምኞት፡ ትርቁ፡ ዘንድ፡ እንግዶችና፡ መጻተኞች፡ እንደመሆናችሁ፡ እለምናችኋለሁ።"

በሃይማኖት : መታነጽ

ኤፌ 2÷20 " በሐዋርያትና በነቢያት : መሠረት : ላይ : ታንጻችኋል:: የማዕዘኑም : ራስ : ድንጋይ : ክርስቶስ : ኢየሱስ : ነው ::" በእርሱም : ሕንጻ : ሁሉ : እየተጋጠመ : በጌታ : ቅዱስ : ቤተ መቅደስ : ለመሆን : ያድጋል:: በእርሱም : እናንተ : ደግሞ : ለእግዚአብሔር : መኖሪያ : ለመሆን : በመንፈስ : አብራችሁ : ትሰራላችሁ::"

ነፍስ : ገዳይ : ማን : ነው?

ዮሐ 8÷44 " እናንተ : ከአባታችሁ : ከዲያቢሎስ : ናችሁ :: የአባታችሁንም : ምኞት : ልታደርጉ : ትወዳላችሁ :: እርሱ : ከመጀመሪያ : ነፍስ : ገዳይ : ነበረ ::"